# የጥቅም ግጭትን ለማስቀረት የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 939/2015"

በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 62 ንዑስአንቀጽ (11) የማንኛውም ድርጅት አባል፣ አመራርና ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የድርጅቱን ጥቅም የማስቀደምና ከእነሱ ጥቅም ጋር እንዳይጋጭ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው የተደነገገ በመሆኑ፤

በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 20 (4) መሰረት ከድርጅቱ የስራ መሪዎች ጋር የስጋ እና የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎች የቦርድ አባል ሆነው እንዳይሰሩ የተከለከለ በመሆኑ፤

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 89 ንዑስአንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

# DIRECTIVE ON AVOIDING CONFLICT OF INTEREST

## DIRECTIVE NO 939/2022

WHEREAS, Article 62, paragraph 11 of Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2019provides that the members, management and employees of any organization have the responsibility of prioritizing the interests of the organization and taking due care not to conflict with their interests while performing their duties;

WHEREAS, according to Article 20 (4) of Proclamation No. 1113/2019, it is forbidden for people who are related by blood or marriage to the company's officials to serve as board members;

NOW THEREFORE, the Civil Society Organizations Authority, as per the powers vested in it under Article 89(2) of the Proclamation, has issued this directive.

**<u>PART ONE</u>**

**<u>GENERAL</u>**

1. **<u>Short title</u>**

ይህ መመሪያ "የጥቅም ግጭትን ለማስቀረት የወጣ መመሪያ ቁጥር 939/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

This Directive may be cited as "Directive No. 939/2022 on Avoiding Conflicts of Interest".

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "ድርጅት" ማለት በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) ትርጓሜ የተሰጠው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው፤

2) "ባለስልጣን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት የተቋቋመው እና የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 (እንደተሻሻለ) የስያሜ ለውጥ በማድረግ የተቋቋመው "የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን" ነው፡፡

3) "የድርጅት አባል" ማለት በድርጅቱ የሥራ አመራርና እንቅስቃሴ የሚሳተፍ የድርጅት አባል ወይም በድርጅቱ ውስጥ በየትኛውም ደረጃ በአመራር ላይ የሚገኝ የቦርድ ወይም የኮሚቴ አባል ወይም የድርጅት ስራ አስኪያጅ፤ የአገር ውስጥ ተወካይን ጨምሮ ማንኛውም የማኔጅመንት አባል፤ የተለያዩ ስራዎችን በሚያከናውኑ ኮሚቴዎች ውስጥ

## 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Directive;

(1) "Organization" means a civil society organization as defined in Article 2 (1) of Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2019;

(2) "Authority" refers to "Civil Society Organizations Authority" which was established in accordance with Article 4 of the Proclamation and was established by Proclamation No. 1263/2022 (as amended) to determine the powers and functions of the executive bodies of the Federal Government by changing its name;

(3) "Member of organization" means an organization member who participates in the management and activities of the organization or a board or committee member or an organization manager who is in leadership at any level in the organization; Any member of management including local

በአባልነት የሚያገለግል ሰው ወይም ማንኛውም የድርጅቱ ሰራተኛ ያጠቃልላል፡፡

4) “ውሳኔ ሰጭ አካል” ማለት በድርጅቱ ውስጥ ከጥቅም ግጭት ጋር በተያያዘ ከድርጅቱ አባላት፣የስራ መሪዎች እና ሰራተኞች ወይም ሌላ ማንኛውም አካል የሚቀርቡ አቤቱታና ጥቆማዎችን የሚያጣራና የሚወስን እንደአግባቡ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ፣ ስራ አስፈጻሚ፣ ቦርድ ወይም ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡

5) “የጥቅም ግጭት” ማለት አንድ የድርጅት አባል ለድርጅቱ ያሉበትን ኃላፊነቶች ገለልተኛና ነፃ በሆነ መንገድ ለማከናወን የማያስችሉት ወይም ያስችሉታል ተብሎ የማይታሰቡ ተጨባጭ ወይም እምቅ ጥቅም ሲኖር ነው፤

6) በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

7) በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴት ፆታንም ይጨምራል፡፡

8) ‘’ግብይት’’ ማለት ለድርጅቱ አገልግሎት የሚውል ማንኛውም የእቃ ወይም የአገልግሎት ግዥና ሽያጭ ማለት ነው፡፡

representative; It includes a person who serves as a member in committees that perform various tasks or any employee of the organization.

(4) "Decision-making body" means the manager, executive, board or general assembly of the organization, which examines and decides on complaints and submissions from the members, leaders and employees of the organization or any other body related to the conflict of interest in the organization.

(5) "Conflict of interest" means when a member of an organization has actual or potential interests that do not allow or are not considered to allow him/her to perform his/her responsibilities for the organization in an independent and free manner;

(6) Definitions given in the Proclamation shall also apply to this directive;

(7) Expressions in the male gender include the female gender.

(8) "Transaction" means any purchase or sale of goods or services for the use of the organization.

3. **የአፈጻጸም ወሰን**

ይህ መመሪያ በማንኛውም የድርጅት አባል ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለጥቅም ግጭት ዓላማና አስተዳደር**

4. **ዓላማ**

የዚህ የጥቅም ግጭት መመሪያ ዓላማ አንድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት የድርጅቱን አባል፣ የስራ መሪ ወይም ሰራተኛ የፋይናንስና ሌላ ማናቸውም የግል ጥቅም ሊያስጠብቅ የሚችል ወይም የድርጅቱን ተጠቃሚነትን አለአግባብ አሳልፎ የሚሰጥ ግብይት፣ ድርድር፣ ዝግጅት ወይም ሌላ ማናቸውም ተጠቃሚነትን በመከላከል የድርጅቱን የላቀ ጥቅም ማስቀደም ነው፡፡

5. **የጥቅም ግጭት መከሰት**

1) የጥቅም ግጭት የሚከሰተው አንድ የድርጅት አባል፣ የስራ መሪ ወይም ሰራተኛ የድርጅቱን ዓላማ ወይም ተልዕኮ ለማሳካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ወይም በሚያከናውነው ተግባር የድርጅቱ ጥቅም ከእርሱ የፋይናንስ ወይም ሌላ ማናቸውም ጥቅም ጋር ግጭት በሚፈጥርበት ጊዜ ነው፡፡

2) አንድ የድርጅት አባል፣ የስራ መሪ ወይም ሰራተኛ የፋይናንስ ወይም ሌላ ማናቸውም ጥቅም አለው

3. **Scope of Application**

This Directive applies to any organization member.

**PART TWO**

**PURPOSE AND MANAGEMENT OF CONFLICT OF INTEREST**

4. **Purpose**

The purpose of this Directive on conflict of interest is to protect the organization's members, leaders or employees from transactions, negotiations, arrangements or any other benefits that may protect the financial or other personal interests of a civil society organization or improperly transfer the organization's interests.

5. **Occurrence of conflict of interest**

(1) A conflict of interest occurs when an organization member, leader or employee creates a conflict with the organization's financial or any other interest in the activities or duties he/she performs to achieve the organization's objectives or mission.

(2) An organization member, executive or employee is said to have a financial or any other interest when the member

የሚባለው አባሉ ወይም የአባሉ ማንኛውም የቤተሰብ አባል በንግዱ፣ በኢንቨስትመንቱ ወይም በሌላ በማናቸውም ግንኙነት ወይም መንገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፤

(ሀ) ከድርጅቱ ጋር ግብይት በሚያካሂደው ወይም ስምምነት በደረሰው ተቋም ውስጥ የባለቤትነት ወይም የኢንቨስትመንት ጥቅም ያለው የሆነ እንደሆነ፤

(ለ) ከድርጅቱ ጋር ግብይት ከሚያካሂደው ወይም ስምምነት ከደረሰው ተቋም ወይም ግለሰብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ስጦታ ወይም ልዩ ጥቅምን ጨምሮ የአገልግሎት ክፍያ የሚያገኝ የሆነ እንደሆነ ነው።

or any member of his/her family, directly or indirectly:

a. has an ownership or investment interest in an institution with which it transacts business or has an agreement;

b. Receives any kind of gift or special benefit from an institution or individual who transacts business with the organization or receives payment for services.

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ አፈጻጸም "የቤተሰብ አባል" ማለት የአባሉ የትዳር ጓደኛ፣ እናት፣ አባት፤ አያት፤ አክስት፣ አጎት፣የአክስት ወይም የአጎት ልጅ፣ አማት፣ ቅድመ አያት፣ ወንድም፣ እህት (ሙሉ ወይም ግማሽ) ፣ ልጅ (ተፈጥሯዊም ሆነ ጉዲፈቻ) ፣ የልጅ ልጅ፣ የልጅ ልጅ ልጅ ፣ የትዳር ጓደኛ ወንድም፣ እህት፣ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ነው፤

(3) For the purpose of the provisions of paragraph 2 of this article, "family member" means the member's spouse, mother, father, grandfather, aunt, uncle, cousin, mother-in-law, great-grandfather, brother, sister (full or half), child (whether natural or adopted), grandchild, grandchild, spouse's brother, sister, child or grandchild.

4) የፋይናንስ ጥቅም መኖር በራሱ የጥቅም ግጭት እንዳለ አያመላክትም። የጥቅም ግጭት ተፈጥሯል የሚባለው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው አካል የጥቅም ግጭት መኖሩን

(4) Having a financial interest does not in itself indicate a conflict of interest. A conflict of interest is said to have arisen when the party making a

ሲያረጋግጥ ነው፡፡

6. **የጥቅም ግጭት መንስዔዎች**

ለጥቅም ግጭት መንስኤ የሚሆን ጥቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከሰት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፤

1) ከድርጅቱ ጋር የሥራ ግንኙነት ባለው ሦስተኛ አካል ውስጥ አክሲዮን ወይም የንብረት ጥቅም መያዝን ወይም ዕዳ መኖርን፤
2) ከድርጅት ጋር የሥራ ግንኙነት ባለው ሦስተኛ አካል ውስጥ የሥራ ባልደረባ ወይም የቦርድ አባል መሆን ወይም በማኔጅመንት መሳተፍ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ራሱ/ወይም የቤተሰብ አባሉ በተቀጣሪነት ማገልገል፤
3) የድርጅቱን ጊዜ፣ ሠራተኛን፣ ቁሳቁስን፣ አቅርቦትን ወይም መልካም ስምን በድርጅቱ ከጸደቁ የሥራ እንቅስቃሴዎች፣ ፕሮግራሞች እና ዓላማዎች ውጭ መጠቀም፤
4) ከድርጅቱ ጋር የሥራ ግንኙነት ካላቸው ሶስተኛ ወገኖች የግል ስጦታዎች መቀበል ወይም ብድር መበደር፤
5) የድርጅት የቦርድ፣ የጠቅላላ ጉባኤ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ በዚያው ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ወይም

decision on the matter confirms the existence of a conflict of interest.

6. **Causes of conflict of interest**

An event that causes a conflict of interest occurs directly or indirectly and includes:

(1) holding shares or property interests or having debt in a third party that has a business relationship with the organization;
(2) being a colleague or a board member in a third party that has a working relationship with the organization or participating in management or in any other way himself or a family member serving as an employee;
(3) use the organization's time, personnel, materials, supplies, or reputation outside of the organization's approved work activities, programs, and purposes;
(4) accepting personal gifts or borrowing loans from third parties who have a working relationship with the organization;
(5) a person who is a member of the board, general assembly or executive committee of an organization, at the same time working as a manager or

ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ መሥራት፤

6) ከድርጅቱ ገቢና ሀብት ለአባላት እንዲሁም ለሠራተኞች በሕግ ከተፈቀደ የአገልግሎት ክፍያ ውጭ ሌላ ክፍያ ሲከፈል፤

7) ከድርጅት ለጋሾች ወይም ተለጋሾች አባላት፣ የስራ መሪዎች ወይም ሰራተኞች ጋር ያለአግባብ የጥቅም ግንኙነት ሲፈጠር፤

8) ከአባላት፣ የስራ መሪዎች ወይም ሰራተኞች ለድርጅቱ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሲቀርብ፤

9) በድርጅት አባልና አዲስ በሚቀጠር ሰራተኛ መካከል ዝምድና መኖር ወይም በድርጅቱ አባላት መካከል ዝምድና መኖር፡፡

employee in the same organization;

(6) when a fee other than the service fee authorized by law is paid to members and employees from the company's income and assets;

(7) when an improper beneficial relationship is created with corporate donors or members of donors, business leaders or employees;

(8) when goods or services are offered to the organization from members, leaders or employees;

(9) Having a relationship between a member of an organization and a newly hired employee or having a relationship between members of the organization.

7. <u>የጥቅም ግጭትን ስለማሳወቅ</u>

1) የጥቅም ግጭት ውስጥ የገባ ወይም የጥቅም ግጭት እንደሚፈጠር የገመተ የድርጅት አባል ይህንኑ ባወቀ ጊዜ ወዲያውኑ ግልጽ በሆነ መንገድ አግባብነት ላለው የበላይ ሀላፊ ወይም የስራ አመራር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በድርጅቱ ውስጥ የጥቅም ግጭት ተፈጥሯል ወይም ሊፈጠር ይችላል ብሎ

## 7. Disclosure of conflict of interest

(1) A member of an organization, who is involved in a conflict of interest or presumes that a conflict of interest will occur, should immediately inform the relevant supervisor or management in a clear manner.

(2) Notwithstanding the provisions of paragraph 1 of this article, any person who believes that a conflict of interest

ያመነ ማንኛውም ሰው ይህንኑ ለድርጅቱ ወይም ለውሳኔ ሰጭ አካሉ ወይም ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይችላል፡፡ በዚህ መንገድ ጥቆማ የደረሰው ድርጅት ወይም ውሳኔ ሰጭ አካል በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8፣ 9 እና 10 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት መርምሮ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3) ባለስልጣኑ ከጥቅም ግጭት ጋር በተያያዘ የቀረበለትን ጥቆማ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጥቆማ ለቀረበበት ድርጅት ይልክለታል፡፡ ድርጅቱ ጥቆማውን መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ ለባለስልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የተላከለትን ጥቆማ ካልመረመረ ወይም መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ አለመስጠቱ በባለስልጣኑ ከታመነበት ባለስልጣኑ በራሱ ጥቆማውን መርምሮ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. <u>የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩን ስለመወሰን</u>

1) ማንኛውም የድርጅት አባል የገንዘብ ወይም ሌላ ማናቸውም ጥቅሙን በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሚሰጠው አካል ቀርቦ ካስረዳ

has arisen or may arise in the organization may report the same to the organization or its decision-making body or authority. The organization or decision-making body that has received such report in this way should investigate and make a decision according to the provisions of Article 8, 9 and 10 of this directive.

**(3)** The authority shall examine the report made to it in relation to the conflict of interest and send the same to the organization to which the report is made to make an appropriate decision. The organization shall investigate the report and inform the authority in writing of its decision.

**(4)** If the organization fails to investigate the report sent to it in accordance with paragraph 3 of this article, or if it is believed by the authority to have failed to make an appropriate decision, the authority may investigate the report itself and make a decision.

## 8. <u>Determining the existence of conflict of interest</u>

**(1)** After any member of the organization presents and explains his financial or any other interest to the decision-making body, a detailed discussion of

በኋላ፣ ግለሰቡ ባልተገኘበት በጉዳዩ ላይ በዝርዝር በመወያየት የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩ ይወሰናል፡፡

the matter in the absence of the individual shall determine whether or not there is a conflict of interest.

2) ውሳኔ ሰጭ አካሉ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ጉዳዩን መርምሮ የተለያዩ አማራጮችን ያካተተ የውሳኔ ሃሣብ የሚያቀርብ ገለልተኛ ሰው ወይም ኮሚቴ ሊሰይም ይችላል፡፡

**(2)** If the decision-making body deems it necessary, it may appoint an independent person or a committee to examine the matter and present a proposal including various options.

3) ውሳኔ ሰጭ አካሉ የፋይናንስ ወይም ሌላ ማናቸውም ጥቅም የተነሳበት ግብይት፣ ድርድር፣ ዝግጅት ወይም ሌላ ማናቸውም ጉዳይ የጥቅም ግጭት ያለበት ወይም የጥቅም ግጭት የማያስነሳ እና ለድርጅቱ የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ መሆን አለመሆኑን በአብላጫ ድምፅ በመወሰን ግብይቱ ወይም ድርድሩ እንዲካሄድ ወይም እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡

**(3)** The decision-making body may decide by majority vote whether a transaction, negotiation, arrangement or any other matter involving a financial or any other interest has a conflict of interest or does not cause a conflict of interest and is in the best interest of the organization, and decide to carry out or cancel the transaction or negotiation.

4) በዚህ መመሪያ የጥቅም ግጭት መንስኤ ሊሆን የሚችል ጉዳይ መሰረት በማድረግ ገለልተኛ መሆኑ ጥያቄ ሊነሳበት የሚችል ማንኛውም የድርጅት አባል የጥቅም ግጭትን በተመለከተ የውሳኔ ሰጭ አካል አባል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡

**(4)** Any member of an organization whose independence may be questioned based on a matter that may be the cause of a conflict of interest may not serve as a member of a decision-making body regarding a conflict of interest.

## 9. የጥቅም ግጭትን ስላለመግለጽ

## 9. Non-disclosure of conflict of interest

1) ውሳኔ ሰጭ አካሉ የድርጅት አባሉ፣የስራ መሪው ወይም ሰራተኛው ያለን ወይም ወደፊት የሚኖርን የጥቅም ግጭትን

(1) If the decision-making body has sufficient reason to believe that the organization member, leader or employee has not fulfilled the

የመግለጽ ግዴታውን አልተወጣም የሚል በቂ ምክንያት ካለው አባሉ የመግለጽ ግዴታውን ያልተወጣበትን ምክንያት እንዲያስረዳ እድል ይሰጠዋል።

2) ውሳኔ ሰጭ አካሉ የድርጅት አባሉን፣ የስራ መሪውን ወይም ሰራተኛውን ምላሽ ካዳመጠ እና እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ምርመራ ካደረገ በኋላ አባሉ፣የስራ መሪውን ወይም ሰራተኛውን ያለን ወይም ወደፊት የሚኖርን የጥቅም ግጭት የመግለጽ ግዴታውን አልተወጣም ብሎ ከወሰነ ተገቢውን የዲሲፕሊን ወይም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል።

3) በዚህ አንቀጽ መሰረት ግዴታውን ባልተወጣ ድርጅት ላይ ባለስልጣኑ አግባብነት ባላቸው ህጎችና መመሪያዎች መሰረት ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

## 10. <u>የስብሰባውን ሂደት በቃለ ጉባዔ ስለመያዝ</u>

ውሳኔ ሰጭ አካሉ በጥቅም ግጭት ሁኔታ ላይ ውሳኔ ሲያስተላልፍ ቃለ ጉባዔ መያዝ ያለበት ሲሆን የስብሰባው ቃለ ጉባዔ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

1) ስብስባ የተካሄደበትን ቀን እና ሰዓት፤

2) በስብስባው የተገኙ አባላትን፤

obligation to disclose any existing or potential conflict of interest, the member shall be given an opportunity to explain the reason for not fulfilling the obligation to disclose.

(2) After the decision-making body listens to the response of the organization member, executive or employee and after conducting further investigation as necessary, it shall take appropriate disciplinary or corrective action if it decides that the member, executive or employee has not fulfilled its obligation to disclose existing or potential conflicts of interest.

(3) In accordance with the relevant laws and regulations, the authority may take appropriate administrative action against the organization that does not fulfill its obligations according to this article.

## 10. <u>Keeping the proceedings of the meeting in minutes</u>

When the decision-making body makes a decision on a conflict of interest, it shall hold a meeting, and the meeting's minutes shall contain at least the following:

1) Date and time of meeting;
2) Members present at the

3) የምልዐተ ጉባዔው መሟላት እና የድምፅ አሰጣጡን፤
4) የጥቅም ግጭቱን የገለጸውን የድርጅት አባል ስም ወይም የፋይናንስ ወይም ሌላ ማናቸውም ጥቅም ያለውን አባል፣
5) የጥቅሙን ዓይነት ወይም ባህርይ፤
6) የጥቅም ግጭቱ በቅድሚያ እንዲታወቅ መደረግ አለመደረጉን፤
7) የጥቅም ግጭቱን መኖር አለመኖሩን ለመወሰን የተወሰዱ እርምጃዎች፤
8) በስብሰባው የተነሱ ጉዳዮች፤
9) ውሳኔ ሰጭው አካል የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖርን በተመለከተ ያስተላለፈውን ውሳኔ፤
10) የቀረቡ አማራጭ መፍትሔዎች (ካሉ) ፤እና
11) ከስብሰባው ራሱን ያገለለ አባል ካለ ስሙንና ምክንያቱን፡፡

meeting;
3) Quorum and voting;
4) The name of the member of the organization who declared the conflict of interest or the member who has financial or any other interest;
5) Type or nature of the interest;
6) Whether or not the conflict of interest was made known in advance;
7) Steps taken to determine whether or not the conflict of interest exists;
8) Matters raised in the meeting;
9) The decision of the decision-making body regarding the absence of conflict of interest;
10) Proposed alternative solutions (if any); and
11) If there is a member who withdraws from the meeting, his name and reason.

## 11.ዓመታዊ መግለጫ

1) እያንዳንዱ የድርጅት አባል ድርጅቱን በሚቀላቀልበት ጊዜ የዚህን መመሪያ ይዘት መረዳቱን እና አክብሮ ለመንቀሳቀስ መስማማቱን በየዓመቱ በጽሑፍ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህ ስምምነት በድርጅቱ ዘንድ መቀመጥ የሚኖርበት ሲሆን

## 11. Annual statement

(1) Each member of the organization must confirm in writing every year that he/she understands the content of this directive and agrees to abide by it at the time of joining the organization. This agreement must be kept by the organization and the non-

ስምምነቱ አለመፈረሙ የመመሪያውን ተፈጻሚነት የሚያስቀር አይሆንም፡፡

2) ማንኛውም ድርጅት ከጥቅም ግጭት ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ኩነቶችን በዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በማካተት ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

signing of the agreement shall not prevent the implementation of the directive.

(2) Any organization should include the incidents related to conflict of interest in the annual performance report and submit the same to the authority.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. የጥቅም ግጭት መመሪያ ስለማውጣት

1) ማንኛውም ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በማይቃረን ሁኔታ ከድርጅቱ የሥራ ባህሪ ጋር የሚስማማ የራሱን የውስጥ ፖሊሲ ማውጣትና የአሰራር ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

3) ባለስልጣኑ እያንዳንዱ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የውስጥ ፖሊሲ ማውጣቱንና የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፡፡

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 12. Issuance of directive on conflict of interest

(1) Any organization should establish its own internal policy and operating system that is consistent with the nature of the organization's work without contradicting this directive.

(2) The authority shall ensure that each organization establishes the internal policy and operating system referred to in paragraph 1 of this article.

### 13. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

የባለስልጣኑ ቦርድ ይህንን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 13. Amendment of the directive

The Board of the authority may amend this directive at any time.

14. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘበ በኋላ በድረገጽ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ጂማ ዲልቦ ደንበል
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር
ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ.ም

**14. Effective date**

This directive shall be effective from the date it is published on website after it has been registered with the Federal Ministry of Justice.

***Jima Dilbo Denbel***
***Director General***
***Authority of Civil Society Organization***
22 December 2022